# በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ መኖር

## መንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔር መንግሥት ግንኙነት

**መግቢያ:-** መንፈስ ቅዱስ እና የእግዚአብሔር መንግስት ያላቸው ግንኙነት ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት በጣም አስፈላጊ ነው።ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔር መንግሥት ግንኙነት **በመዳን ላይ፣ በልውጠት ላይ** እና **በተለዕኮ ስራ ውስጥ** ያለውን የእግዚ አብሔርን ሥራ **በቅጡ እንድንረዳና በመጸሐፍ ቅዱስ መሰረት ላይ እንድንቆም የሚያደርገን ነውና**።በመንፈስ ቅዱስና በእግዚአብሔር መንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት በ ጣም ጠንካራ ነው። መንፈስ ቅዱስ **የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ እንዲገለጥ፣ እ ንዲመሠረት**፣ እና **በሰዎች ውስጥ መለኮታዊ ኃይል እንዲታወቅ የሚያደርገው** እንዲሁም **ሰ ወችን የእግዚአብሔር መኖሪያ የሚያድርጋቸው** እርሱ ስልሆነ።

### 1. መንፈስ ቅዱስ መንግሥቱን ይገልጣል ያጸናግል

የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት የእግዚአብሔር ርስትና አገዛዝ ነው።እንዲሁም በሰማይም ሆነ በምድር ፈቃዱ የሚፈጸምበት ሁኔታና ቦታ ነው ። **(ማቴ 6፥10)**። መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው።ስለሆነም በኃይል መንግሥቱን በሰዎች ልብ እና ሕይወት ውስጥ ያመጣል። **ሉቃ 11፥20** ኢየሱስ አለ፡-“እኔ በእግዚአብሔር ጣት አ ጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፣ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግስት ወደእናንተ **ደርሳለች**።” በማቴ 12፥28 ፡-“ እኔ **በእግዚአብሔር መንፈስ** አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግስት ወደእናንተ **ደርሳለች**። ”ይህ የጌታ ንግግር ***መንፈስ ቅዱስ የሚሠራበት ቦታ መንግሥቱ የተገለጠበት ቦታ መሆኑን ያረጋግጣል ነው።***

### 2. መንፈስ ቅዱስ እንደ የመንግሥት ዜጎች እንድንኖር ያበረታታናል

መንግሥቱ የወደፊት ነገር ብቻ አይደለም። በመንፈስ የተወለዱ ሰዎች ውስጥ አሁን ያለ እውነ ት ነው። **ዮሐ 3፥5** – ኢየሱስ አለ፡- “ከውሃና ከመንፈስ ያልተወለደ ሰው ወደ መንግሥቱ መግ ባት አይችልም።” መንፈስ ቅዱስ አዲስ ልደትን ይሰጣል ማለትም በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ መዳን ማግኘት ነው። **ቲቶ 3:5** ይህም ሰዎችን ወደ መንግሥቱ ውስጥ ያስግባል።መንፈስ ቅዱስ የዳነውን አማኝ፡- **ያድርበታል፣ ለቤዛ ቀን ያትመዋል፣ይቀድሰዋል፣ወደ እውነት ሁሉ ይመራዋል፣ያስተምረዋል፣ ያጽናናዋል፣የስጋን ስራ መግድል ያስችለዋል፣የመንግስቱን ወንጌል እንዲሰብክ መንፈሳዊ ስጦታን ይሰጠዋል፣ በኀይል ይሞላዋል.......ወዘተ።**

## 3. መንፈስ ቅዱስ የመንግሥቱን ባህሪ ያሳያል

መንግሥቱ መንፈሳዊ ባህሪ ነው ያለው ።ከዚህ የተነሳ ዋጋ የሚሰጠው ለጽድቅ፣ለቅድስና፣ለወንድማማች መዋድድ፣ለእግዚአብሔር ፈቃድ መፈጸምና ከዓለም ፈጽሞ ስለመለየት እና በአንጻሩ በመንፈስ መመላለስን የሚጠይቅ ነው። **ሮሜ 14፥17** በአጠቃላይ የእግዚአብሔር መንግሥት መብላትና መጠጣት መገለጫ ባህሪው አይደለም። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ የሚፈጸም ጽድቅ ሰላም እና ደስታ ነው።እነዚህ የመንግስቱ ባህሪያት በሰው ጥረት አይመጡም። መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ህይወት ውስጥ እንዲፈሩ ያድርጋችዋል እንጂ።**ገላ 5፥22–23።** መንፈስ ቅዱስ የመንግሥቱን ሕይወት በውስጣችን ይፈጥራል።